# የንብ ቀፎ ሥራ ጨረታ ማስታወቂያ

ኢትዮ ዌትላንድስና ናቹራል ሪሶርስ አሶሴሽን (EWNRA) ሀገር በቀል የልማት ድርጅት ሲሆን፤ ማህበረሰብ ተኮር ለሆነ የጋጣ ንብ ማንባት ስራ አገልግሎት የሚዉል በቁጥር 340 (ሶስት መቶ አርባ) ኬንያ ቶፕ ባር ሞዴል የንብ ቀፎ በጨረታ አወዳድሮ ማሰራት ይፈልጋል።

ስለዚህ በእንጨትና ብረታ ብረት ስራ ህጋዊ ፈቃድ ያላቸውና ከታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ አካላት የጨረታዉን ሰነድ ከረቡዕ, ሚያዝያ 16 እስከ አርብ, ግንቦት 02 2016 ዓ.ም ባሉት ተከታታይ ቀናት ዘወትር በስራ ሰዓት አዲስ አበባ ከተማ ከሚገኘው ኢትዮ ዌትላንድስና ናቹራል ሪሶርስ አሶሴሽን (EWNRA) ዋና መስሪያ ቤት ወይም ቤንች ሸኮ ዞን ሚዛን-አማን ከተማ ከሚገኘው የድርጅታችን ጽ/ቤት በመቅረብ በብር 100 (አንድ መቶ) በመግዛት መወዳደር የሚችሉ መሆኑን እየገለጽን ተወዳዳሪዎች የጨረታዉን ሰነድ በሰም በታሸገ ኢንቨሎፕ በማሸግ ለጨረታ ማስገቢያ ታስቦ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ አዲስ አበባ ከተማ በሚገኘው ኢትዮ ዌትላንድስና ናቹራል ሪሶርስ አሶሴሽን (EWNRA) ዋና መስሪያ ቤት እንዲያስገቡ እያሳሰብን፣ ጨረታው የሚዘጋው ሰኞ, ግንቦት 05 2016 ዓ.ም ከቀኑ በ8:30 ሲሆን የጨረታዉ ሳጥን ከቀኑ 8:30-9:00 ሰዕት ድረስ ታሽጎ ይቆያል። ጨረታው ተወዳዳሪዎች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸዉ በተገኙበት በተመሳሳይ እለት ማለትም ሰኞ, ግንቦት 05 2016 ዓ.ም ከቀኑ በ9:00 ሰዓት አዲስ አበባ ከተማ በሚገኘው ኢትዮ ዌትላንድስና ናቹራል ሪሶርስ አሶሴሽን (EWNRA) ዋና መስሪያ ቤት የሚከፈት መሆኑን እንገልጻለን።

በጨረታዉ ለመወዳደር መሟላት ያለባቸዉ መስፈርቶች (ቅድመ ሁኔታዎች)

- በእንጨትና ብረታብረት ስራ ለ 2016 ዓ.ም የታደሰ ህጋዊ የሙያ ፈቃድ ያለዉ
- የዘመኑን ግብር የከፈለ
- በንብ ቀፎ ስራ ህጋዊ እውቅና ካለው ገጠር ቴክኖሎጂ ማሰልጠኛ የሰለጠነና ማስረጃ ማቅረብ የሚችል።
- ካሁን በፊት ለሰራባቸዉ ተመሳሳይ ሥራዎች ማለትም ኬንያ ቶፕ ባር ሞዴል ባለፍሬም የንብ ቀፎ ስራ ከ3 በላይ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል።
- የሚቀርበው የንብ ቀፎ ሥራ ዋጋ **ሸካ ዞን በአንደራቻ ጌጫ ከተማ** ወረዳ ድረስ የማጓጓዣ ዋጋን ታሳቢ ያደረገ መሆን አለበት
- የተጨማሪ እሴት ታክስ/ቫት ተመዝጋቢ የሆነ
- የጨረታ ማስከበሪያ ጨረታ ከገባበት ጠቅላላ ዋጋ መጠን 10% የሚሆን ሲፒኦ (CPO) በባንክ ማስያዝ የሚችል

- ❖ በድርጅቱ አቅራቢነት የሚገባውን የውል ስምምነት ህጎች የሚያከብር፤ ስራውን ጥራቱን በጠበቀ መልኩ ውል ከተገባበት ቀን ጀምሮ ሁለት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ሰርቶ የሚያስረክብ
- ❖ ጨረታውን አልፎ ወደ ውል ስምምነት የሚገባ ተጫራች ለቅድመ ክፍያ ዋስትና (Advance guarantee) የሚሆን ለሁለት ወራት ጸንቶ የሚቆይ ውል ከገባበት መጠን 30% የሚሆን የባንክ ዋስትና ደብዳቤ ወይም ሲፒኦ (CPO) ድርጅቱ በሚያስቀምጥለት የጊዜ ገደብ ውስጥ ማቅረብ/ማስያዝ የሚችል

ተጨማሪ ዝርዝር መረጃ አዲስ አበባ ከተማ ከሚገኘው ኢትዮ ዌትላንድስና ናቹራል ሪሶርስ አሶሴሽን (EWNRA) ዋና መስሪያ ቤት ወይም ቤንች ሸኮ ዞን ሚዛን ከተማ ከሚገኘው ድርጅታችን ጽ/ቤት በአካል በመቅረብ ወይም በስልክ ቁጥር 011-5527791/047-3350634/047-335-0874 ማግኘት የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ማሳሰቢያ

**ድርጅቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታዉን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ በህግ የተጠበቀ ነዉ፡፡**